# የውኃ
# ጥምቀት

ጽሑፍ፡- በቲም ፊሎስ
ትርጉም፡- በግርማዊ
እርማት፡ ይግረም ረታ

አሳታሚ

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት
የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ.ሣ.ቁጥር 127፣ አዲስ አበባ

ይህ በራሪ ወረቀት ለቤተ ክርስቲያን ምእመናን ከእግዚአብሔር ቃል ጠቃሚ እውነቶችን ከሚያስተላልፉ ተከታታይ እትሞች ውስጥ አንዱ ነው። እነዚህ በራሪ ወረቀቶች የቀረቡት ከአማርኛ ውጭ በሌሎች ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ሰዎች በሚረዱበት መንገድ ቀለል ተደርገው ነው። ምእመኟ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል እስካልተገነዘቡ ድረስ የትኛዋም ቤተ ክርስቲያን ልትጠነክር አትችልም። መንፈስ ቅዱስ እነዚህን በራሪ ወረቀቶች ተጠቅሞ የእግዚአብሔር ሕዝብ የማይለወጡትን የእግዚአብሔር እውነቶች እንዲረዱ እንዲያግዝ ጸሎታችን ነው። ይህንን በራሪ ወረቀት በሚገባ ለመጠቀም፣ የተጠቀሱትን ጥቅሶች አውጥተህ ልታነብ ይገባል።

**Water Baptism**
**Printed by SIM Press**

# ክርስቲያኖች በውኃ የሚጠመቁት ለምንድን ነው?

አንድ ጊዜ ከአራት የተለያዩ ቤተ እምነቶች የተውጣጡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ ጥምቀት በሚያምኑባቸው አሳቦች ላይ ለመወያየት ተሰባሰቡ። ከመሪዎች አንዱ፣ «አንድ ሰው፤ እውነተኛ ደኅንነትን ለማግኘት መጠመቅ ይኖርባቸዋል ብለን እናምናለን» ሲል ተናገረ። ሌላው መሪ፣ «የቤተ ክርስቲያን አባላት መሆናቸውን ለማሳየት የአማኞች ልጆች መጠመቅ አለባቸው ብለን እናምናለን» አለ። ሦስተኛውም ግለሰብ፣ «ጥምቀት ሁሉም ክርስቲያን ሊታዘዘው የሚገባው ሥርዓት እንደሆነ እናምናለን። ጥምቀት አንድ ሰው እውነተኛ አማኝ መሆኑን፤ ከእንግዲህ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል እንደሆነና የጌታን እራት ለመቀበል የሚችልበት ደረጃ ላይ እንደደረሰ ያሳያል» ሲል ተናገረ። አራተኛው የቤተ ክርስቲያን መሪ፣ «በጥምቀት ላይ ብዙም ትኩረት አናደርግም። አንድ ሰው ለመጠመቅ ከፈለገ እናጠምቀዋለን። ነገር ግን አንድን ሰው ሊያድን ወይም በመንፈሳዊ ሕይወቱ ላይ ምንም ሊጨምር ስለማይችል በጣም አስፈላጊ ነው ብለን አናስብም» ሲል ገለጸ።

ዛሬ አብያተ ክርስቲያናት በጥምቀት ጉዳይ ላይ የተለያየ አመለካከት አላቸው። ብዙ ክርስቲያኖች ጥምቀት አስፈላጊ እንዳልሆነ በማሰብ ይህንኑ ተግባር ከመፈጸም ይቆጠባሉ። ሌሎች ደግሞ ያልተጠመቀ ክርስቲያን እውነተኛ ደኅንነት እንዳላገኘ ያስባሉ። ብዙ ክርስቲያኖች ደግሞ የጥምቀትን ሥርዓት ቢፈጽሙም ለምን እንደተጠመቁ አያውቁም። የተጠመቁት ቤተ ክርስቲያናቸው አስፈላጊ መሆኑን ስለተናገረች ብቻ ነው።

ነገር ግን፣ «የእግዚአብሔር ቃል ስለ ጥምቀት ምን ያስተምራል?» የሚለውን አስፈላጊ ጥያቄ ማንሣት አለብን:: ይህ አጭር በራሪ ወረቀት የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጥምቀት ምን እንደሚያስተምርና ዛሬ ለምን መጠመቅ እንዳለብን እንድናውቅ ነው:: በተጨማሪም፣ ክርስቲያኖች በአሳብ የሚለያዩባቸውን ጥቂት የውኃ ጥምቀት አሳቦችን እንመለከታለን::

## ክፍል አንድ፣ የጥምቀት ትርጉም

### 1. የክርስትና ጥምቀት እንዴት ተጀመረ?

### ሀ. አይሁዶች ጥምቀትን ያካሂዱ ነበር::

ክርስቶስ በዚህ ዓለም አገልግሎትን ከመጀመሩ በፊት መጥምቁ ዮሐንስ ተከታዮቹን ያጠምቅ ነበር (ማቴ. 3:5-11):: አይሁዶች ኃጢአታቸውን በመናዘዝ ሊጠመቁ እንደሚገባቸው ሰብኳል:: መሢሐቸው ለሆነው የክርስቶስ መምጣት በመዘጋጀት የተለወጠ ሕይወት መምራት ያስፈልጋቸው ነበር:: ስለሆነም፣ የጥምቀት ሥርዓት የተጀመረው ከክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት በፊት ነበር:: ነገር ግን ምሁራን ዮሐንስ የጥምቀትን አሳብ ከየት እንዳገኘው የተለያየ አሳብ አላቸው:: ዮሐንስና ኢየሱስ ተከታዮቻቸውን የማጥመቅ አሳብ ያገኙባቸው ሦስት የተለያዩ ምንጮች አሉ::

1. በብሉይ ኪዳን አይሁዶች በቤተ መቅደስ እግዚአብሔርን ከማገልገላቸው በፊት ይታጠቡ ነበር (ዘዳ. 30:17-21):: እግዚአብሔር አይሁዶች እርሱን በሚያገለግሉበት ጊዜ ሁሉ እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን መታጠብ እንዳለባቸው ተናግሮ ነበር:: ካህናት እግሮቻቸውን የሚታጠቡት የእግዚአብሔርን ሕጎች እንደሚጠብቁ ለማሳየት ነበር:: እጆቻቸውንም



የሚታጠቡት በሥራዎቻቸውና በአገልግሎታቸው እግዚአብሔርን ለማስከበር መፈለጋቸውን ለማሳየት ነበር:: ውኃው የእጆቻቸውንና የእግሮቻቸውን ቆሻሻ እንደሚያጥብ ሁሉ፣ በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ልብና ሕይወት ሊራቸው ይገባ ነበር:: በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ አይሁዶች ይህንን ልማዳዊ የመታጠብ ሥርዓት ልክ አንድ ሰው ኃጢአቱን ሲናዘዝ እግዚአብሔር ያንን ኃጢአተኛ የሚያነጻበትን ዓይነት ምሳሌ ነበር ይጠቀሙ የነበረው:: ለዚህ ነበር ንጉሥ ዳዊት፣ «ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፣ ከኃጢአቴም አንጻኝ. . . በሂሶጵ እርጨኝ፣ እነጻማለሁ፤ እጠበኝ፣ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ» ያለው (መዝ. 51:2፣7):: ውጫዊ የሆነ በውኃ መታጠብ አንድን ሰው ከኃጢአት ሊያነጻው አይችልም:: ውኃ መንፈሳዊ የሆነውን ኃጢአት ሊያነጻ አይችልም:: ነገር ግን ውኃ አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ይቅርታና መንፈሳዊ መንጻት በሚጠይቅበት ጊዜ የሚሆነውን ሁኔታ እንደ ምሳሌ ያሳያል::

2. በክርስቶስ ዘመን ብዙውን ጊዜ የአይሁዶችን ሃይማት ለመከተል የሚፈልጉ አሕዛብ ይጠመቁ ነበር:: ጥምቀት ከእግዚአብሔር የራቁት አሕዛብ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ለመሆን መቻላቸውን የሚያሳይ ነበር::

3. በክርስቶስ ዘመን፣ አንዳንድ የአይሁድ የሃማኖት ቡድች አዳዲስ አባሎቻቸው እንዲጠመቁ ጠየቋቸው:: ይህም አሮጌው ሕይወታቸው እንደሌለ የሚያሳይ ምልክት ነበር:: አዲስ አማኞች በአዲሱ ማኅበረሰብ ውስጥ ደንቡን ጠብቀው ለመኖር ቃል ይገባሉ::

የአይሁዶች የጥምቀት ሥርዓት ሀ) ከኃጢአት መንጻትና ለ) በተለወጠ ሕይወት አዲሱን ማኅበረሰብ

ለመቀላቀል የቀድሞ ሕይወቱን የተወን ሰው ያመለክቱ ነበር።

**ለ. መጥምቁ ዮሐንስ ተከታዮቹን አጥምቋል።** ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ለሰው ልጆች ኃጢአት ለመሞት ከሰማይ ከመምጣቱ በፊት እግዚአብሔር የሰዎችን ልብ ያዘጋጅ ዘንድ መጥምቁ ዮሐንስን ልኮታል (ሉቃ. 3:1-18)። ዮሐንስም እየሰበከና እያነጋገራቸው ሰዎች ለክርስቶስ መምጣት እንዲዘጋጁ ጠይቋቸዋል። ከዚያም ሕይወታቸውን ለመለወጥ የፈቀዱትን ሰዎች ወንዝ ውስጥ አጥምቋቸዋል። መጥምቁ ዮሐንስ መልእክቱን ለመስማትና እርሱን ለመከተል የፈለጉትን ሰዎች ያጠመቀበትን ሁኔታ ከሚከተሉት እውነቶች እንመለከታለን።

1. የዮሐንስ ጥምቀት ግልጽና ሕዝብ የሚመለከተው ሥርዓት ነበር። ይህም ሥርዓቱን ለሚያዩት ሰዎች ሁሉ የሚጠመቀው ግለሰብ በሕይወቱ ውስጥ ትልቅ ለውጥ እንዳደረገ የሚያሳይ ምስክርነት ነበር።

2. የዮሐንስ ጥምቀት የግለሰቡን የኃጢአት ኑዛዜና የእግዚአብሔርን ይቅርታ መፈለጋቸውን ያሳያል። ለዚህም ነው ዮሐንስ «ለኃጢአት ይቅርታ የንስሐን ጥምቀት እንደሰበከ» የተጻፈው (ሉቃ. 3:3)። የውኃ ጥምቀት ኃጢአታቸውን በማጠብ ይቅርታን አላስገኘላቸውም። ነገር ግን የውኃ ጥምቀቱ ኃጢአታቸውን ተናዝዘው ንስሐ ለገቡት ሰዎች እግዚአብሔር የሰጣቸውን የውስጥ ንጽሕና በምሳሌነት ያሳያል።

3. ዮሐንስ እውነተኛ ንስሐ የተለወጠ ሕይወትን ማሳየት እንደሚገባው ገልጿል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ



ንስሐ ኃጢአት በመሥራታችን መጸጸታችንን ብቻ አያመለክትም። እውነተኛ ንስሐ እግዚአብሔርን በሚያስደስት መልኩ ለመኖር እንችል ዘንድ ተግባራችንን ለመለወጥ መወሰናችንንም የሚያመለክት ነው። ዮሐንስ ሕይወታቸውን ለመለወጥ እውነተኛ ውሳኔ ሳያደርጉ ከብዙ ሰዎች ጋር በመቀላቀል ሊጠመቁ የመጡትን ሰዎች አላጠመቃቸውም (ሉቃስ 3:7-14)።

4. የዮሐንስ ትምህርት ያተኮረው ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ በሚጀመረው የእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ነበር። «የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» (ማቴ. 3:2) እያለ ያስተምር ነበር። መጥምቁ ዮሐንስ ክርስቶስ የአይሁዶች ንጉሥ በመሆን ወዲያውኑ በዚህ ዓለም መንግሥቱን የሚጀምር መስሎት ነበር። ስለሆነም፣ ሰዎች የዚሁ የክርስቶስ ምድራዊ መንግሥት አካል ለመሆን መንፈሳዊ ሕይወታቸውን እንዲያዘጋጁ ጠይቋቸዋል። ጥምቀት አንድ ሰው እግዚአብሔርን የሚያሳዝነውን ጥሩ ያልሆነ ነገር ትቶ የመሢሑን መንግሥት ለመቀላቀል እንደሚፈልግ ያመለክት ነበር። ዮሐንስ ክርስቶስ የመንፈሳዊ መንግሥት ንጉሥ እንደሆነ አልገባውም ነበር። ጥምቀት የክርስቶስን መንፈሳዊ መንግሥት ለመቀላቀል የሚፈልጉ ሰዎች አሮጌው ሕይወታቸው ማብቃቱን ለማሳየት የሚፈጽሙት ሥርዓት ነው። አማኞቹ ክርስቶስን መንፈሳዊ ንጉሣቸው አድርገው ለመከተልና የአማኞች ማኅበረሰብ አባል ለመሆን ሙሉ በሙሉ ፈቃደኞች ነበሩ።

5. በመጨረሻም፣ መጥምቁ ዮሐንስ መሢሑ ከእርሱ የውኃ ጥምቀት የበለጠ ጥምቀት የሚያካሂድ እንደሆነ ገልጿል። ኢየሱስ ተከታዮቹን «በመንፈስ

ቅዱስና በእሳት» እንደሚያጠምቅ አስረድቷል (ሉቃስ 3:16):: ይህም ዮሐንስ ክርስቶስ መጥቶ መንግሥቱን በሚጀምርበት ጊዜ የውኃ ጥምቀቱ፣ ከዚያ በላይ የሆነውን ጥምቀት ማለትም የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት እንደሚያመለክት ያስተማረ መሆኑን የሚያሳይ ይመስላል:: ክርስቶስ ለሚከተሉት ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ይሰጣል:: የውኃ ጥምቀቱ መንፈስ ቅዱስ ወደ አማኞች እንዲመጣ ምክንያት አይሆንም፣ ነገር ግን ኢየሱስ ለተከታዮቹ መንፈስ ቅዱስን እንደሰጠ የሚያመለክትበት ውጫዊ ምሳሌ ነው:: (ስለ መንፈስ ቅዱስ በቅርቡ የሚወታውን የዚህን ጽሑፍ ተከታታይ ቢመለከቱ የበለጠ ግንዛቤ ያገኛሉ::)

**ሐ. የመጥምቁ ዮሐንስን ምሳሌ በመከተል፣** ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ለመከተል ፈቃደኛ የሆኑትን ሰዎች አጥምቀዋል (ዮሐ. 3:22፤ 4:1-2)::

## 2. ክርስቲያናዊ ጥምቀት ማለት ምን ማለት ነው?

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ቤተ ክርስቲያን የመጥምቁ ዮሐንስን መሠረታዊ የጥምቀት ግንዛቤ እንደተቀበለች እንመለከታለን:: በዮሐንስ የጥምቀት ትምህርት ላይም አንዳንድ አሳቦችን ጨምረዋል:: አዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ሁሉ እንዲጠመቁ ያዛል (ማቴ. 28:19-20፤ የሐዋ . 2:38):: ነገር ግን ክርስቶስ ሳይገባን ይህንን ትእዛዝ እንድንፈጽም ብቻ ሳይሆን ምክንያቱንም እንድንገዳ ይፈልጋል::

አዲስ ኪዳን የውኃ ጥምቀት ምሳሌያዊ ተግባር መሆኑን ያስተምራል:: ተምሳሌት (ምልክት) አንድን የጠለቀ፣ የተሰወረና መንፈሳዊ ትርጉም የሚያብራራ ግልጽ ተግባር ወይም የትምህርት መርጃ መሣሪያ ነው:: ለምሳሌ፣ በቅዱስ ቁርባን ጊዜ «እንጀራ» የክርስቶስን አካል ሲያሳይ፣ «ወይኑ» ደግሞ ደሙን ያመለክታል:: እንጀራውን መብላታችን ውስጣዊ መንፈሳዊ ሕይወታችን ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመልን ተግባር ላይ እንደሚደገፍ ያስረዳል:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የውኃ ጥምቀትም ብዙ አስፈላጊና የማይታዩ መንፈሳዊ እውነቶችን የሚያብራራ ውጫዊ ተግባር ነው:: አዲስ ኪዳን በጥምቀት የሚከተሉትን ነገሮች በአደባባይ ማወጃችንን ይናገራል::

**ሀ) በጥምቀት ጊዜ ክርስቶስን ለመከተል መወሰናችንን በአደባባይ እናውጃለን::** በአዲስ ኪዳን፣ ብዙውን ጊዜ አዳዲስ አማኞች በሌሎች ሰዎች ፊት ይጠመቁ ነበር:: በሰዎች ፊት በምንጠመቅበት ጊዜ ለሌሎች ክርስቲያኖችና በስፍራው ለተገኙት ሌሎች ሰዎችም ክርስቶስን ለመከተል ሙሉ በሙሉ መወሰናችንን ማወጃችን ነው:: ጥምቀት ሊካሄድ የሚገባው ሰዎች ክርስቶስ ማን እንደሆነ በትክክል ከገባቸውና በመስቀል ላይ በመሞት ደኅንነታቸውን የገዛ ጌታቸው እንደሆነ ከተረዱ በኋላ ሊሆን ይገባል::

**ለ. ጥምቀት ከኃጢአታችን መንጻታችንን በምሳሌነት ያሳያል** (ቲቶ 3:5-6፤ 1ኛ ጴጥ. 3:21-22):: ውኃ ሰውነታችንንና ልብሶቻችንን ከቆሻሻ እንደሚያነጻ ሁሉ፣ ጥምቀትም የኃጢአታችንን መታጠብ ያሳያል:: ይህም የሆነው በክርስቶስ ባመንን ጊዜ ነው:: ውኃው ኃጢአታችንን እንደሚያነጻው ግልጽ ነው:: ነገር ግን ጥምቀት በክርስቶስ ባመንን ጊዜ በሕይወታችን ውስጥ የተፈጸመውን ሁኔታ የሚገልጽ ውጫዊ ምሳሌ ነው:: ለዚህም ነው ጴጥሮስ አስፈላጊው ነገር ውኃውና ውጫዊ ቆሻሻን የማስወገዱ

ተግባር ሳይሆን፣ በክርስቶስ ላይ ካለን እምነት የሚመነጩ የመልካም ሕሊና ውጤቶች እንደሆኑ የሚያስረዳው።

**ሐ. ጥምቀት መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበልንና አሁን የክርስቶስ አካል መሆናችንን ያሳያል** (ዮሐ. 7:37-39፣ 1ኛ ቆሮ. 12:13)። ከመጥምቁ ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ የጥምቀት ተግባር መንፈስ ቅዱስ ወደ አማኞች ከመምጣቱ ጋር የተያያዘ ሆኖ ቆይቷል (ማቴ. 3:11)። እውነተኛ አማኝ የሆነ ሁሉ በውኃ ብቻ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስም ተጠምቋል። የውኃ ጥምቀት መንፈስ ቅዱስን ወደ ሕይወታችን አያመጣውም። ነገር ግን በክርስቶስ በማመናችን ምክንያት በመንፈስ ቅዱስም እንደተጠመቅን ያሳያል።

ይህም መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ያልነበርነውን ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች እንዳደረገን ያስረዳል (ዮሐ. 1:12፤ ሮሜ 8:13-17)። በተጨማሪም፣ መንፈስ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን፣ ማለትም ክርስቶስን እንደ አዳኛቸውና ጌታቸው የሚከተሉ ማኅበረሰብ አባላት አድርጎናል። ጳውሎስ ይህንን የአማኞች ማኅበረሰብ «የክርስቶስ አካል» ሲል ይጠራዋል። ስለሆነም፣ ጥምቀት የዓለምን ማኅበረሰብ ትተን ከእግዚአብሔር ቤተሰብ መቀላቀላችንን ያሳያል። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12:12-26 እና በኤፌሶን 4:1-6 እንዳስተማረው፣ በመንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ አካል ክፍሎች ስለሚያደርገን ከሌሎች አማኞች ጋር አንድነትን መፍጠር አለብን። መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠንን የጸጋ ስጦታዎች በመጠቀም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳችን ሌላውን የማገልገል ኃላፊነት አለብን።



ስለሆነም፣ ጥምቀት የክርስቶስ ተከታዮች የሆኑት አዲስ ማኅበረሰብ አካል መሆናችንን ያሳያል። ክርስቶስን በአካሉ፣ ማለትም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማገልገል ራሳችንን አሳልፈን እንሰጣለን። ይህም ክርስቶስን ለማገልገል የቤተ ክርስቲያናችን ትጉሕ አባላት እንደምንሆን ያስረዳል። ሰዎች የውኃ ጥምቀት ከወሰዱ በኋላ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ወይም ትጉሕ አገልጋይ አለመሆናቸው የእግዚአብሔር ፍላጐት አይደለም።

**መ. በጥምቀት የክርስቶስ ሞት፣ መቀበር፣ ትንሣኤና ዕርገት ተካፋዮች መሆናችንን እናውጃለን** (ሮሜ 6:1-14፣ ቆላ. 2:11-12፤ 3:3-4፤ ገላ. 2:20)። ጳውሎስ አንድ ክርስቲያን በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ በመንፈሱ ከክርስቶስ ጋር እንደሚያያዝ አስተምሯል። ይህም አንድ አናጢ ሁለት የእንጨት ቁራጮችን በማጣበቂያ ከሚያያይዝበት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለቱ ቁራጮች አንድ እንጨት ይሆናሉ። በእግዚአብሔር ዓይኖች፣ እያንዳንዱ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር የተያያዘ በመሆኑ፣ ክርስቶስ ያለፈበትን የሕይወት ልምምድ ይለማመዳል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት እኛም በመስቀል ላይ ሞተናል። ኢየሱስ በተቀበረ ጊዜ እኛም ከእርሱ ጋር በመቃብር ውስጥ ነበርን። ክርስቶስ ከሞት ሲነሣ እኛ ም ከሞት ተነሥተናል። አሁን ኢየሱስ በሰማይ ስለሚገኝ እኛም በሰማይ እንገኛለን (ኤፌ. 2:6)።

የዚህ ከባድ እውነት ትርጉም፣ ከክርስቶስ ጋር በሞትን ጊዜ የሚቆጣጠረንና ኃጢአትን እንድንሠራ የሚያስገድደን ነገር ሁሉ ሞቷል ማለት ነው። (ይህ አንድ ሰው ሲሞት ለተበደረው የገንዘብ ዕዳ ተጠያቂ አይሆንም እንደ ማለት ነው።) ስለሆነም፣ ኃጢአትን እንድንሠራ የሚያስገድደን የሰይጣንና የኃጢአት

ባሕርይ ተሰብሯል:: ከክርስቶስ ጋር ከሞት በመነሣታችን እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሕይወት የምንኖርበትን አዲስ መንፈሳዊ ችሎታ ከመንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶናል:: ኃጢአትን ልንሠራ ብንችልም፣ ከእንግዲህ ኃጢአት ሊቆጣጠረን እንደማይችል ጳውሎስ ገልጿል:: ይልቁንም እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ነፃ ወጥተናል::

ጥምቀት ይህንን እውነት ያስረዳል:: ኢየሱስ ወደ መቃብር እንደ ወረደ ሁሉ እኛም ወደ ውኃው ዝቅ ብለን እንገባለን:: እርሱ ከመቃብር እንደ ተነሣ ሁሉ፣ እኛም ከውኃው እንወጣለን:: ስለሆነም፣ መንፈሳዊ ትንሣኤ ያገኘን አዲስ ሰዎች መሆናችንን ለሌሎች እንመሰክራለን:: በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለአሮጌው አኗኗራችን፣ ለኃጢአታችንና የሰይጣንን መንገድ በመከተሉ ተግባር ሞተናል:: በጥምቀት፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በቅድስና ለመመላለስና እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ለመኖር መምረጣችንን እናውጃለን:: ኢየሱስ አሁን በእኛ በኩል ሕይወቱን እየኖረ ነው:: የራስ--ወዳድነት ፍቃዳችን እኛንና ምርጫችንን እንዳይመራ በምናደርግበት ጊዜ፣ ኢየሱስ ለእኛ ኃይልን በመስጠት ሕይወቱን በእኛ በኩል ይኖራል:: መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት እንዴት እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሕይወት መኖር እንዳለብን በሚያስተምረን ጊዜ ከሰማነው፣ በንጽሕና እንኖራለን::

## 3. ክርስቲያኖች ሁሉ መጠመቅ አለባቸው?

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ የእግዚአብሔር ቃል ጥምቀት ለእያንዳንዱ ክርስቲያን በጣም አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል:: ክርስቲያኖች ሁሉ መጠመቅ እንደሚገባቸው የሚያስረዱ ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ::



ሀ. የክርስቶስንና የሐዋርያትን ትእዛዛት ለመጠበቅ ስንል እንጠመቃለን (ማቴ 28:19-20፤ የሐዋ. 2:38):: ክርስቶስ ለተከታዮቹ ከሰጣቸው የመጨረሻዎቹ ትእዛዛት በአንዱ፤ ደቀ መዛሙርቱ በዓለም ሁሉ ለሚኖሩ ኃጢአተኞች የመሞቱን ዜና እንዲናገሩ አዟቸዋል:: ሰዎችም በኢየሱስ በሚያምኑበት ጊዜ «በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም» መጠመቅ ይኖርባቸዋል:: በሐዋርያት ሥራ ውስጥ፣ ሰዎች በኢየሱስ ባመኑ ጊዜ ወዲያውኑ ይጠመቁ ነበር (የሐዋ. 8:12፤ 36-38፤ 10:47-48፤ 16:31-34)::

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች የመጠመቅ ወይም ያለመጠመቅ መብት እንዳላቸው አያስተምርም:: ለመጠመቅ ፈቃደኛ አለመሆን ወይም ለብዙ ጊዜ ሳይጠመቁ መቆየት ከኢየሱስ ትእዛዛት አንዱን ያለመታዘዝ ተግባር ነው:: ኢየሱስ፣ «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» ብሏል (ዮሐ. 14:15):: ኢየሱስን የምንወድ ተከታዮቹ እንደ መሆናችን፣ ልንታዘዘው እንፈልጋለን:: ለዚህም ነው አሥራታችንን በመክፈል፣ ጉረቤቶቻችንን በመውደድ፣ ዝሙትን ባለመፈጸም ወይም የሌሎችን ንብረት ባለመስረቅ የምንታዘዘው:: በተጨማሪም፣ ኢየሱስ በመጠመቅ እርሱን ለመከተል ቁርጥ ውሳኔ ማድረጋችንን በአደባባይ እንድንመሰክር ይፈልጋል:: ይህንንም ትእዛዝ መጠበቅ ይኖርብናል::

ለ. በሕዝብ ፊት በምንጠመቅበት ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ውስጥ አንድ ጠቃሚ ነገር ይከናወናል:: መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቲያኖች እምነት ለሌሎች የሚታይና ግልጽ መሆን እንዳለበት ያስጠነቅቃል (ሉቃ. 9:26፤ 12:8-9፤ ሮሜ 10:9-10):: ይህ የአደባባይ ጥምቀት የሚደርስብን ስደት ቢኖር

እንኳን ኢየሱስን በደቀ መዝሙርነት ለመከተል መቁረጣችንን በድጋሚ ያረጋግጣል:: ብዙ ክርስቲያኖች የሚጠመቁት ክርስቶስን ለመከተል ከልባቸው በወሰኑበት ወቅት እንደነበር ይመሰክራሉ:: ከመጠመቃችን በፊት ከፊል ማንነታችን ኢየሱስን ለመከተል ሲፈልግ የተቀረው ደግሞ ዓለምን ለማስደሰት እንደሚፈልግ ዓይነት ይመስላል:: ነገር ግን ለመጠመቅና ጌታን ለመታዘዝ ለምን እንደምንጠመቅና መታዘዝ ምን ማለት እንደሆነ ሲገባን ያን ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ እንደ ኢየሱስ ተከታዮች ሙሉ በሙሉ የተሰጠ ሕይወት እንድንኖር ያበረታታናል::

ሐ. ጥምቀት ለማያምኑ ሰዎች ትልቅ ምስክርነት ነው:: ቤተ ክርስቲያንና የሚጠመቀው ሰው ጥምቀትን በግልጽ በሚያሳዩበት ወቅት፣ በስፍራው ተገኝተው የሚመለከቱ ዓለማውያን ወንጌሉን በግልጽ ይረዳሉ:: አማኞች ለደኅንነታችን በኢየሱስ ሞት ላይ እንደምንደገፍና ኢየሱስን ለመታዘዝ መወሰናችንን ያያሉ::

ማጠቃለያ:- ተጠምቀሃል? ካልሆነ፣ ለምን? ኢየሱስ የግል አዳኝህ እንደሆነ ካመንህ የኢየሱስን ትእዛዝ ለመፈጸም ስትል መጠመቅ አለብህ:: ነገር ግን የጥምቀትን ምንነት መረዳትህን ማረጋገጥ አለብህ:: ወደ ውኃው ስትገባ፣ ኢየሱስ ኃጢአታህን እንዳጠበልህ መግለጽህ ነው:: የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ለመሆን ራስህን አሳልፈህ መስጠትህ ነው:: እንዲሁም ለአሮጌው ማንነትህና የኃጢአተኝነት አኗኗርህ ጀርባህን በመስጠት ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ሕይወት ለመኖር ቃል መግባትህ ነው:: ለእግዚአብሔር ክብር በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለማገልገል ራስህን መስጠትህ ነው::



የተጠመቅኸው በልጅነትህ ከሆነ፣ ጥምቀት ለደኅንነትህ ዋስትና እንደማይሆን መረዳት አለብህ:: (ክፍል ሁለትን ተመልከት::) ደኅንነትን ልታገኝ የምትችለው ኢየሱስ ለኃጢአቶችህ በመስቀል ላይ በመሞት ለደኅንነትህ ዋጋ እንደከፈለ በግልህ ስታምን ብቻ ነው::

ሁላችንም በዕለታዊ አኗኗራችን በጥምቀት የተገለጸውን እውነት ተግባራዊ እንድናደርግ ጌታ ይርዳን:: ኃጢአታችን ይቅር ተብሏል በሚል ልበ ሙሉነት እንድንኖር ጌታ ይርዳን:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እየተከተልንና እርሱን በደስታ እያገለገልን እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ እንድንኖር ጌታ ይርዳን:: አሜን!

## ክፍል ሁለት: ስለ ውኃ ጥምቀት አንዳንድ አነጋጋሪ ጉዳዮች

አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ስለ ውኃ ጥምቀት መሠረታዊ ትምህርቶችን ይቀበላሉ:: ነገር ግን ዝርዝር እምነቶችና ልምምዶች ከቤተ እምነት ቤተ እምነት ይለያያሉ:: ከእነዚህም ልዩነቶች አንዳንዶቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ አደገኛ ትምህርቶችን ይጨምራሉ:: ለምሳሌ ያህል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደኅንነት መንገድ ምን እንደሚያስተምር በትክክል የማያውቁ ወገኖች አሉ:: እነዚህ ሰዎች አንድ ሰው ሙሉ ደኅንነትን ለማግኘት መጠመቅ አለበት ይላሉ:: ነገር ግን የውኃ ጥምቀት እንደማያድነን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያሳያል:: ጥምቀት ሕጻናትን እንደሚያድን ወይም ለአዋቂዎች የኃጢአትን ይቅርታና ደኅንነት እንደሚያስገኝ የሚያስተምሩ ሰዎች ተሳስተዋል:: (ከታች ጥያቄ 1ን ተመልከት::) ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጥምቀትን በተመለከተ

በግልጽ ያልተብራሩ ሌሎች ጉዳዮች አሉ:: እነዚህ የተለያዩ ግንዛቤዎች ከእኛ የተለየ አስተሳሰብ ካላቸው አብያተ ክርስቲያናት ጋር ኅብረትን እንድናቋርጥ ወይም በጥላቻ እንድንመለከት የሚያደርጉ ዋነኛ ችግሮች አይደሉም:: ክርስቲያኖች በአሳብ ከሚለያዩባቸው ጉዳዮች መካከል አንዳንዶቹ ከዚህ በታች ቀርበዋል::

## 1. ጥምቀት ደኅንነትን ያስገኛል?

አንዳንድ ክርስቲያኖች ማር. 16:16፣ ዮሐ. 3:5፣ የሐዋ. 2:37-38 እና 1ኛ ጴጥ. 3:20-21ን በመጥቀስ፣ አንድ ሰው እስካልተጠመቀ ድረስ ደኅንነትን አላገኘም ይላሉ:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጥምቀት እንደማያድነን በግልጽ ተቀምጧል:: (ደኅንነት እኛ በምንሠራው ሥራ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ እንደሚገኝ ጳውሎስ ያብራራውን ሙሉ አሳብ ከሮሜ 1-5 እና ገላትያ 1-3 አንብብ::) ጥምቀት ደኅንነትን እንደማያስገኝ የአዲስ ኪዳን ምሳሌዎች ያሳያሉ::

ሀ. ጳውሎስ አንድ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ደኅንነት ለማግኘት ሊያከናውን የሚችለው ሥራ እንደሌለ ያስረዳል (ኤፌ. 2:8-9):: ለመዳን ልናደርግ የሚገባው ነገር ቢኖር እምነታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በመጣል የእግዚአብሔርን ነፃ ስጦታ መቀበል ብቻ ነው:: የምንድነው በጥምቀት ቢሆን ኖሮ ደኅንነት ነፃ ስጦታ ሳይሆን የሥራችን ውጤት በሆነ ነበር::

ለ. ደኅንነት በጥምቀት ላይ ቢመሠረት ኖሮ በመስቀል ላይ የነበረው ሌባ ሊድን ባልቻለም ነበር:: ነገር ግን ሌባው ለመጠመቅ ሳይችል ቢሞትም ኢየሱስ የዘላለምን ሕይወት ሊያገኝ እንደሚችል ቃል ገብቶለታል (ሉቃ. 23:40-43)::



ሐ. ጥምቀት ለደኅንነት አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ፣ ኢየሱስና ጳውሎስ የወንጌል አገልግሎታቸው አንዱ ክፍል አድርገው ጥምቀትን ያላካሄዱት ለምንድን ነው? (ዮሐ. 4:2፤ 1ኛ ቆሮ. 1:14-17):: ጥምቀት ለአድማጮቻቸው ደኅንነት አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ የአገልግሎታቸው አንዱ ክፍል ያደርጉት ነበር:: ጳውሎስ የደኅንነት መልእክት የሆነውን ወንጌል፣ ክርስቲያኖች በኢየሱስ በማመናቸው ምክንያት ሕይወታቸው እንደተለወጠ ለማሳየት ከሚያካሂዱት የጥምቀት ሥርዓት ይለየዋል::

ኢየሱስ ሐዋርያቱ ተከታዮቹን እንዲያጠምቁ ያደረገበት ምክንያት ወደፊት ለሚጠብቃቸው አገልግሎት ሥልጠና ለመስጠት አስቦ ይሆናል:: ጳውሎስ አማኞች በእርሱ መንፈሳዊ «አባትነት» ላይ እንዳይደገፉ በመፍራት አብዛኞቹን የቤተ ክርስቲያን አባላት አላጠመቀም:: ጳውሎስ ምእመናን ኢየሱስ መንፈሳዊ አለቃቸው እንደሆነ እንዲመለከቱና ከአጥቢያ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መንፈሳዊ ምሪቶችን እንዲቀበሉ አስተምሯል:: የአጥማቂው ማንነት ብዙም አስፈላጊ አልነበረም:: ነገር ግን ጳውሎስ በኢየሱስ ማመናችንና እርሱን ለመከተል መወሰናችንን በጥምቀት መግለጻችን አስፈላጊ መሆኑን አስረድቷል::

### ጥምቀት ሰውን ያድናል የሚል መልእክት የሚያስተላልፉ የሚመስሉትን ጥቅሶች እንዴት ልንረዳቸው ይገባል?

ሀ. ማር. 16:16 እምነትና ጥምቀት በአንድነት ደኅንነትን እንደሚያስገኙ ይናገራል:: ይህ የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን እነዚህ ሁለት ተግባራት በአንድ ላይ ስለመፈጸማቸው የነበራትን መረዳት ያንጸባርቃል:: (ማብራሪያውን ከታች ተመልከት::) ማርቆስ «ያላመነ

ግን ይፈረድበታል» አለ እንጂ፣ «ያልተጠመቀ ይፈረድበታል» አላለም:: ይህም ደኅንነትን የሚያስገኘው ቁልፍ ተግባር እምነት እንጂ መጠመቅ እንዳልሆነ ያሳያል::

ለ. የሐዋ. 2:38 ንስሐና ጥምቀት በአንድ ላይ ደኅንነትን እንደሚያስገኙ ያስረዳል:: ጴጥሮስ ሰዎች ደኅንነትን ለማግኘት ከጥምቀት በፊት ንስሐ መግባት እንዳለባቸው በግልጽ አመልክቷል:: በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ከሚገኙ ጥቅሶች አብዛኞቹ ጥምቀትን ሳይጠቅሱ በኢየሱስ ማመን ደኅንነትን እንደሚያስገኝ ያስረዳሉ (የሐዋ. 10:43፤ 13:38-39፤ 26:17-18)፡፣ ንስሐንና ይቅርታን በአንድ ጊዜ ያነሡ ነበር :: ጴጥሮስ እምነትን፡ ጥምቀት ለደኅንነት አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ሁልጊዜም ጥምቀትን፣ ንስሐንና ጥምቀትን «ደኅንነት» በተባለው አንድ ተግባር ውስጥ ካካተተባቸው ምክንያቶች አንዱ በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ብዙውን ጊዜ እነዚህ ሦስቱ ተግባራት በተመሳሳይ ጊዜ ይፈጸሙ ስለነበር ነው:: ለምሳሌ ያህል፣ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባና የፊልጵስዩስ የወኅኒ ጠባቂ በኢየሱስ ባመኑበት ቅጽበት ተጠምቀዋል (የሐዋ. 8:34-38፤ 16:31-34):: በሐዋርያት ሥራ 16:31-34፤ ጳውሎስ ለወኅኒ ቤቱ ጠባቂ ለመዳን ምንን ማመን እንዳለበት ነግሮታል:: በዚህ ስፍራ ጳውሎስ ጥምቀትን አልጠቀሰም:: ጥምቀት ለደኅንነት አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ ጳውሎስ ሳይጠቅሰው አያልፍም ነበር::

ሐ. ዮሐንስ 3:5 ኢየሱስ ለደኅንነት ወይም የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየት አንድ ሰው ዳግም መወለድ እንዳለበት አሳስቧል (ዮሐ. 3:3):: ኢየሱስ ዳግም ለመወለድ ሁለት ዓይነት ልደት



አስፈላጊ መሆኑን ገልጿል:: <u>የመጀመሪያው</u>፣ «ከውኃ መወለድ» ሲሆን፣ <u>ሁለተኛው</u> «ከመንፈስ» መወለድ ነው (ዮሐ. 3:5):: ነገር ግን ውኃ ምንን እንደሚያመለክት በዚህ ምንባብ ውስጥ የተገለጸ ነገር የለም:: የውኃ ጥምቀትን ማለቱ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን የተቀረው የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ደኅንነትን የውጫዊ ተግባራችን ውጤት ሳይሆን በክርስቶስ በማመን የሚገኝ እንደሆነ በግልጽ ስለሚያሳይ (ለምሳሌ፣ ዮሐ. 3:16)፣ ይህ ክፍል የሚሳየው የውኃ ጥምቀትን አይመስልም:: አንዳንድ ምሁራን ውኃ ሥጋዊ ልደትን ያሳያል ይላሉ:: አንድ ሰው ደኅንነትን ለማግኘት መጀመሪያ ትንሽ ልጅ ሆኖ መወለድ አለበት:: (ልጅ በሚወለድበት ጊዜ በማኅፀን ውስጥ ልጁን ከብቦት የቆየው ውኃ ይፈስሳል::) ከዚያም መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ስጦታ ሊያጐናጽፈን ይሠራል:: ሌሎች ምሁራን ውኃና መንፈስ ቅዱስ አንድን ነገር፣ ማለትም አንድ ሰው በሚድንበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ የሚያመጣውን መንፈሳዊ ልደት እንደሚያመለክቱ ያስረዳሉ (ዮሐ. 7:37-39):: ወይም ደግሞ የመጥምቁ ዮሐንስን አገልግሎት ሊያመለክት ይችላል:: ለኒቆዲሞስና ለአይሁዶች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት የብሉይ ኪዳንን ልምምዶች መከተሉ ብቻ በቂ አልነበረም:: ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ንስሐ ሊገቡና የዮሐንስን ወይም የኢየሱስን ጥምቀት ሊቀበሉ ይገባ ነበር:: ከዚያ በኋላ መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ልደትን ይሰጣቸዋል:: አንድን ሰው ሊያድንና አዲስ ፍጥረት ሊያደርግ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው:: ኢየሱስ ውኃ ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ዘንድ የተለያየ አሳብ ቢኖርም፣ ጠቅላላውን አዲስ ኪዳን በምንመለከትበት ጊዜ ክርስቶስ የውኃ ጥምቀት

ደኅንነትን እንደሚያስገኝ እያስተማረ አለመሆኑን እንረዳለን::

መ. 1ኛ ጴጥ. 3:20-21 ለመረዳት በጣም የሚያስቸግር ምንባብ ነው:: ይህንን ምንባብ ደኅንነት ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ብቻ ሊገኝ እንደሚችል በሚያስተምሩ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አማካኝነት በጥንቃቄ ልንተረጉመው ይገባል:: በዚህ ምንባብ ውስጥ የሚከተሉትን ነጥቦች እናያለን:: <u>በመጀመሪያ</u፣ ጴጥሮስ ውኃ ኖኅንና ቤተሰቡን «እንዳዳነ» ይናገራል:: ቀድሞውኑ ጻድቅ ለነበረው ለኖኅ የጥፋት ውኃው መንፈሳዊ ደኅንነትን እንዳላስገኘለት ግልጽ ነው (ዘፍጥ. 6:8-9):: ነገር ግን እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተሰቡን ከጥፋት ውኃው በአካላዊ ሁኔታ እንዳዳናቸው፣ የጥፋት ውኃውንና መርከቡን ተጠቅሞ በሰላም ከአራራት ተራራ ላይ እንዳሳረፋቸው እናውቃለን:: <u>ሁለተኛ</u>፣ ጴጥሮስ የኖኅ ዘመኑ የጥፋት ውኃ ከጥምቀት ውኃ ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ያስረዳል:: በሁለቱም ሁኔታዎች ውኃ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከሚሰጠው ደኅንነት ጋር ተያይዟል:: ይህ ደኅንነት ከአደጋ የመትረፍን አካላዊ ደኅንነት ወይም ከኃጢአት የመዳንን መንፈሳዊ ደኅንነት ሊያመለክት ይችላል:: <u>ሦስተኛ</u>፣ ጴጥሮስ በውኃ የመጠመቁ አካላዊ ተግባር መንፈሳዊ መንጻትንና መንፈሳዊ ደኅንነትን ያስገኛል ማለቱ አይደለም:: ጴጥሮስ የሚናገረው አካላዊ ቆሻሻን ወይም ሥነ ምግባራዊ ኃጢአቶችን ስለሚያስወግድ መታጠብ ሳይሆን፣ ለእግዚአብሔር ስለሚኖረን መልካም ሕሊና መሆኑን ያስረዳል::

ጴጥሮስ በቀላል የጥምቀት ሥርዓት ላይ ከማተኮር ይልቅ ሰዎች እምነታቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንዲያሳርፉ እግዚአብሔር



የሚፈልግባቸው መሆኑን ያብራራል:: ይህም እምነትን፣ ንስሐ መግባትንና መጠመቅን ያካትታል:: አማኞች በሚጠመቁበት ጊዜ የኃጢአት ይቅርታ ስላገኙ እርሱን በሚያስከብር መንገድ ለመኖር መወሰናቸውን ለእግዚአብሔር ማስታወቃቸው ነው:: ጴጥሮስ ይህንን ቃል ኪዳን «ለእግዚአብሔር መልካምን ሕሊና ማሳየት» ሲል ይገልጸዋል:: ጴጥሮስ አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ ከኃጢአቱ እንደሚድን አስተምሯል:: ከዚያም አማኞች እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ለመኖር ራሳቸውን አሳልፈው ይሰጡና ይህንኑ መስጠት በጥምቀት አማካኝነት ይገልጹታል::

ስለሆነም፣ ለደኅንነት ወይም የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን መጠመቅ አስፈላጊ ነው ብሎ ማመን ወይም ማስተማር ትክክል አይደለም:: ነገር ግን አማኞች የኢየሱስን ትእዛዝ ለመፈጸምና እግዚአብሔርን በሕይወታቸው ውስጥ የፈጸመውን ተግባር በተምሳሌትነት ለማሳየት መጠመቅ እንዳለባቸው ማስተማር ይኖርብናል:: (ከላይ 3ኛውን ነጥብ ተመልከቱ::)

## 2. አንዳንድ ክርስቲያኖች «በኢየሱስ ስም» ብቻ የሚያጠምቁት ለምንድን ነው?

በማቴዎስ 28:19 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ፣ «በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም» እንዲያጠምቁ በግልጽ አዝዟቸዋል:: አንድ አይሁዳዊ በኢየሱስ ወይም በእግዚአብሔር ስም እንደ ተጠመቀ ሲናገር፣ ክርስቶስን ወይም እግዚአብሔርን ለመከተልና ለመታዘዝ ወስኗል ማለት ነው:: ኢየሱስ ሥላሴ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተገለጠው መሠረት፣ ደቀ መዛሙርቱ አዳዲስ አማኞችን

በሥላሴ አምላክ «ስም» እንዲያጠምቁ አዝዟቸዋል፡፡ ለሥላሴ አምላክ በመታዘዝ ሕይወታችንን መምራት አለብን፡፡ ነገር ግን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ «በኢየሱስ ስም» ስለመጠመቅ ያስተማረው ለምንድን ነው፡፡

በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ለአይሁዶች ትልቁ ማሰናከያ በእግዚአብሔር አብ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ማመን አልነበረም፡፡ ነገር ግን አይሁዶች እነርሱ የሰቀሉት ኢየሱስ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ልጅ መሆኑን አምነው ለመቀበል ተቸግረው ነበር፡፡ ስለሆነም፣ ሐዋርያት የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች (አይሁዶች፣ ሳምራውያን፣ በፍልስጥኤም የነበሩት አሕዛብና የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት) በተለይ በኢየሱስ ስም እንዲጠመቁ ጠየቁ፡፡ ሐዋርያት ደኅንነት ሊገኝ የሚችለው ለሰዎች ኃጢአት ሲል በሞተውና የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ በማመን እንደሆነ አጥብቀው ለማሳሰብ ፈልገው ነበር፡፡ በእግዚአብሔር አብ ብቻ ማመኑ ከእንግዲህ ሰውን ሊያድን አይችልም፡፡ አማኙ ኢየሱስ ከአብ ጋር እኩል የሆነ አምላክ መሆኑን ማመን ያስፈልገው ነበር፡፡ አማኙ ይህንኑ ኢየሱስ አምላክና አዳኙ የመሆኑን እውነት «በኢየሱስ ስም» በመጠመቅ ይገልጻል፡፡

ማቴዎስ በጻፈው ደብዳቤ የቤተ ክርስቲያንን የተሟላ ትምህርት ሲገልጽ፣ ጥምቀት በሥላሴ ስም እንጂ በኢየሱስ ስም ብቻ መሆን የለበትም ብሏል፡፡

(ማስታወሻ፣ የኢየሱስ «ስም» የሚለው ሐረግ ራሱ ኢየሱስን የሚያመለክት የአይሁዶች አገላለጽ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ እንደ ያህዌ፣ አዶናይ፣ ኤልሻዳይ የሚሉ የእግዚአብሔር ስሞች የእግዚአብሔርን የተለያዩ የባሕርይ ገጽታዎች



በማሳየት ራሱን እግዚአብሔርን ያመለክታሉ፡፡ ስለሆነም፣ የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ «ስም» ስትጸልይ ወይም ስታጠምቅ፣ ተግባሯ በኢየሱስ ጌትነት፣ አዳኝነትና የእግዚአብሔር ልጅነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን መግለጿ ነበር፡፡ ለደቀ መዛሙርቱ ሥልጣንን የሰጣቸው ጌታቸው የሆነው ኢየሱስ ነበር፡፡ በኢየሱስ ስም የሚጠመቀው ግለሰብ ከኃጢአቱ ንስሐ የገባ ነበር፡፡ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው በሆነው በኢየሱስ ላይ እምነቱን በመጣል እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ተቀብሎታል፡፡ ጌታው የሆነውን ኢየሱስን በደቀ መዝሙርነት ለመከተል እንደወሰነም በጥምቀት አማካኝነት በአደባባይ ይመሰክራል፡፡)

መጽሐፍ ቅዱስ አንዱ አምላክ ሦስት አካላት እንደሆነ በግልጽ ያስተምራል፡፡ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሆኖ ራሱን ገልጿል፡፡ ይህንን በጥምቀት ላይ መግለጹ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም፣ ዛሬ በጥምቀት ጊዜ የአብን፣ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ስም መጠቀም ይኖርብናል፡፡

### 3. አንዳንድ ክርስቲያኖች ልጆችን የሚያጠምቁት ለምንድን ነው?

የልጆች ጥምቀት አብያተ ክርስቲያናት የሚወዛገቡበት አከራካሪ ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ጉዳይ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ክፍፍልን ሊፈጥር እንደማይገባ መገንዘቡ ጠቃሚ ነው፡፡ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጥምቀት የሚያስተምረውን ለመረዳት በጥንቃቄ ቃሉን ማጥናት ይኖርባታል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ሕገ ደንቧን ካወጣች በኋላ ግን በጥምቀት ላይ የተለየ አመለካከት ያላቸውን ቤተ እምነቶች መቃወም

የለባትም። መንፈስ ቅዱስ አንድ ሰው እንዴትና መቼ መጠመቅ እንዳለበት ለቤተ ክርስቲያን ነጻነት የሰጠ ይመስላል። ይህ ባይሆን ኖሮ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማን መጠመቅ እንዳለበትና መቼ መጠመቅ እንዳለበት በግልጽ ያብራራልን ነበር።

ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ልጅን ማጥመቅ ለዘላለም ደኅንነትን ያስገኝለታል ብሎ የሚያምን የለም። ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ለደኅንነት አንድ ሰው በኢየሱስ ማመን እንዳለበት ያስተምራሉ። እንዲህ ከሆነ፣ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ሕፃናትን የሚያጠምቁት ለምንድን ነው?

ሀ. አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ሕፃናትን ማጥመቅ ሕፃናቱ ከአዳም የወረሱትን የኃጢአት ኩነኔ ለማስወገድ ይረዳል ይላሉ (ሮሜ 1:18፤ 5:12-19)። ልጁ አድጎ በኢየሱስ እስኪያምን ድረስ ከእግዚአብሔር ፍርድ ይጠብቀዋል። ልጁ ካደገ በኋላ ጥምቀቱ ዘላቂ መንፈሳዊ በረከት እንዲያስገኝለት በኢየሱስ ማመን አለበት።

ለ. ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጥምቀት አማኞች የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት መሆናቸውን እንደሚያመለክት ያስተምራሉ። ይህም በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ጥላ ሥር እንደሚኖር ያሳያል ይላሉ። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል የመሆን ምልክቱ ግርዛት ነበር (ዘፍጥ. 17: 9-14)። በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ቤተሰብነት ምልክት ጥምቀት እንደሆነ ያምናሉ። 1ኛ ቆሮንቶስ 7:14 ክርስቲያን ቤተሰቦች በልጆቻቸውና በእግዚአብሔር መካከል እንዴት ልዩ ግንኙነት እንደሚመሠርቱ ያስረዳል። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የአማኞች ልጆች የእግዚአብሔር ቤተሰብ መሆናቸውን ለማመልከት ሲሉ ልጆችን ያጠምቃሉ።



በተጨማሪም፣ ጥምቀቱ ከንቱ እንዳይሆን ልጅ በሚያድግበት ጊዜ በኢየሱስ እንዲያምን ያስተምራሉ። እምነታቸው «መረጋገጥ» አለበት።

ሕፃናትን የሚያጠምቁ አብያተ ክርስቲያናት ቤተሰቡ «ሁሉ» ተጠመቁ (የሐዋ. 16:33) በሚለው አሳብ ላይ በመመሥረት በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ሕፃናትም ሳይጠመቁ እንዳልቀሩ ያስረዳሉ። ነገር ግን የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ለማመን ከሚያስችል ዕድሜ ላይ ያልደረሱትን ልጆች እንዳጠመቀች ወይም እንዳላጠመቀች የሚያረጋግጥ ግልጽ ማስረጃ ማቅረብ አይቻልም።

ሐ. አዲስ ኪዳን ሕጻናት መጠመቅ አለባቸው ብሎ እንደማያስተምር የሚገነዘቡ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ወላጆች ልጆቻቸውን በመንፈሳዊ መንገድ ለማሳደግ በጉባኤ ቃል መግባታቸው ጠቃሚ ነው ይላሉ። ሐና ሕጻኑ ሳሙኤልን ለእግዚአብሔር አሳልፋ እንደሰጠች ሁሉ፣ ምእመናን ልጆቻቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው ይሰጣሉ (1ኛ ሳሙ. 1:28)። በዚህም ልጃቸው ኢየሱስን እንዲከተል ለማስተማር ቃል ይገባሉ። ሌሎች ምእመናንም ወላጆች ይህንኑ ጠቃሚ ኃላፊነት ለመወጣት እንዲያግዟቸው ይበረታታሉ።

አዲስ ኪዳን ሕፃናትን ስለ ማጥመቅ ግልጽ መመሪያዎችን አይሰጥም። ነገር ግን አዋቂዎች በኢየሱስ በሚያምኑበት ጊዜ እንዲጠመቁ ያዛል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ግልጽ ሆኖ የሚገኘው የውኃ ጥምቀት አዋቂዎችን ያካተተ ነበር። መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጥምቀት ምሳሌ አዋቂዎች ካመኑ በኋላ ኢየሱስን ለመከተል ቁርጥ ውሳኔ ማድረጋቸውን የሚገልጹበት ነው። ቤተ ክርስቲያን ልጆችን ለማጥመቅ ከመረጠች እያደጉ ሲሄዱ

ጥምቀት እንደማያድናቸው በግልጽ ማስተማር አለባት:: ልጆቹ ሲያድጉ በግላቸው ካላመኑ በስተቀር የልጅነት ጥምቀታቸው እንደማያደናቸው ወላጆችንም ማስተማር ያስፈልጋል:: የውኃ ጥምቀት ጥቅም ሊሰጥ የሚችለው አንድ ሰው በኢየሱስ ካመነና እርሱን ለመከተል ሕይወቱን ከሰጠ ብቻ ነው::

## 4. አዲስ ክርስቲያን መቼ መጠመቅ አለበት? ልጆችስ በስንት ዓመታቸው መጠመቅ አለባቸው?

ሕፃናትን የማያጠምቁ አብያተ ክርስቲያናት አዳዲስ ክርስቲያኖችንና ልጆችን መቼ እንደሚያጠምቁ የሚመሯቸው ሦስት ነጥቦች አሉ::

በመጀመሪያ፣ ክርስቲያኖች እንዳመኑ ወዲያውኑ መጠመቅ አለባቸው:: ከሐዋርያት ሥራ ውስጥ የምንመለከተው ምሳሌ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አዳዲስ ክርስቲያኖች ወንጌሉን እንደተገነዘቡና ኢየሱስን ለመከተል እንደወሰኑ በሚረዱበት ጊዜ፣ ያጠምቋቸው እንደነበር ያስረዳል:: አንድ ክርስቲያን የውኃ ጥምቀትን ችላ በሚልበት ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ኢየሱስን ለመከተል አለመፍቀዱን ያሳያል::

ሁለተኛ፣ ወንጌሉና ውሳኔያቸው በግልጽ ይብራራ ዘንድ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች የአጭር ጊዜ ትምህርት መስጠቱ መልካም ነው:: ይህ አጭር ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ከግለሰቡ ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ እንዲመለከቱ ዕድል ይሰጣቸዋል:: መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ለመኖር በሚመጣበት ጊዜ ለእግዚአብሔር አዲስ ፍቅር እንዲኖረው ስለሚያደርግና ባሕርዩን ስለሚለውጥ፣ አዲሱ አማኝ በሕይወቱ እነዚህን ነገሮች ያሳያል::



ሦስተኛ፣ ልጆች ኃጢአተኞች መሆናቸውንና ኢየሱስ ለኃጢአታቸው እንደ ሞተ ለመረዳት በሚችሉበት ጊዜ፣ ሊጠመቁ ይችላሉ:: የአማኞችም ልጆች ሳይቀሩ ለደኅንነታቸው በኢየሱስ ለማመን የግል ቃል ኪዳን መግባት አለባቸው:: በዚህም ጊዜ እንደ ማንኛውም አዲስ አማኝ መጠመቅ አለባቸው::

## 5. ሰዎችን ማጥመቅ የሚቻልበት ተገቢው ዘዴ የትኛው ነው?

ሌላው ክርስቲያኖች በአሳብ የሚለያዩበት ጉዳይ፣ «ሰዎችን ማጥመቅ የሚቻልበት ተገቢው ዘዴ የትኛ ው ነው?» የሚለው ነው:: ሙሉ በሙሉ ውኃ ውስጥ መነከር አለባቸው? ወይስ ከላያቸው ላይ ውኃ ማፍሰስ ያሻል? ወይስ ውኃ መርጨት ይገባል? መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን አንድ ዓይነት የጥምቀት ዘዴ እንድትከተል በግልጽ ስላልተናገረ፣ ክርስቲያኖች በዚህ ጉዳይ ላይ ሊከፋፈሉ አይገባም:: «ጥምቀት» የሚለው ቀዳሚ ቃል ለየትኛውም ዓይነት ጥምቀት (ለመንከርም ሆነ ለመርጨት) ሊያገለግል ይችላል:: የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን የተለመደ አሠራር በመንከር ማጥመቅ ይመስላል:: የዮሐንስም የክርስቶስም ደቀ መዛሙርት ተከታዮቻቸውን በዮርዳኖስ ወንዝ አጥምቀዋቸዋል:: ያጠመቁበት ሁኔታ ባይገለጽም፣ በመንከር ሳይሆን እንደማይቀር እንገምታለን:: ከኢየሱስ ጋር መቀበራችንንና መነሣታችንን በብቃት የሚያብራራው ይሄኛው ዓይነት ጥምቀት ብቻ ነው:: ነገር ግን ጥምቀት በቤት ውስጥ በተካሄደበት ወቅት (የሐዋ. 10:47-48፤ 16:33) የተጠቀሙት የጥምቀት ዘዴ ሊሆን ይችላል የተጠቀሙት:: አማኞች ለጥምቀት ወደ ወንዝ መውረዳቸው ስላልተጠቀሰ፣ የጥምቀት ዓይነቶችን መወሰኑ አስቸጋሪ ይሆናል:: አስፈላጊው ነገር

የጥምቀቱ ተምሳሌትነት እንጂ ጥምቀቱ የተካሄደበት መንገድ አይደለም።

## 6. በሕጻንነታቸው ወይም ደኅንነትን ከማግኘታቸው በፊት የተጠመቁ ሰዎች እንደገና መጠመቅ ይኖርባቸዋል?

በሕፃንነቱ የተጠመቀ ሰው ኢየሱስን ለመከተል ከወሰነ በኋላ እንደገና መጠመቅ አለበት? ደኅንነትን ከማግኘቱ በፊት የተጠመቀ ግለሰብስ? ቤተ ክርስቲያን በሌሎች ቤተ እምነቶች የተጠመቁ ሰዎችን አባሎቿ ለማድረግ እንደገና እንዲጠመቁ ልትጠይቅ ይገባል? እነዚህ ዛሬ ክርስቲያኖች የሚያነሡዋቸውና መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ምላሽ ያልሰጠባቸው ጥያቄዎች ናቸው። ስለሆነም፣ የምንሰጠው ምላሽ የተሻለ ነው ብለን የምናስበውን ነው። አቋማችን ፍጹማዊ እውነት ነው ብለን በማሰብ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ልንጋጭ አይገባም። እያንዳንዱ ቤተ እምነት እነዚህን ጥያቄዎች በጥንቃቄ በማጥናት ወደ ራሱ ማጠቃለያ ሊደርስ ይገባል። አብያተ ክርስቲያናት የእምነት አንቀጾችን በሚነድፉበት ጊዜ የሚከተሉትን አሳቦች ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

ሀ. አዲስ ኪዳን ይህን ሁኔታ እንዴት ልንመለከተው እንደሚገባን ሁለት ምሳሌዎችን ይሰጣል። <u>በመጀመሪያ፣</u> በሐዋርያት ሥራ 8:13-24 ስምዖን የተባለው ግለሰብ ተጠምቋል። በኋላ እንደታየው ግን በተጠመቀ ጊዜ ልቡ በእግዚአብሔር ፊት ቅን አልነበረም። በመሆኑም፣ ጴጥሮስ ንስሐ እንዲገባ ጠንከር ያለ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶታል። ነገር ግን ጴጥሮስ ስምዖን ንስሐ ከገባ እንደገና መጠመቅ እንዳለበት አልገለጸም። ይህም ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል በማመን እውነተኛ አማኝ



ያልሆነን ሰው ካጠመቀች በኋላ ግለሰቡ በትክክል በሚያምንበት ጊዜ እንደገና ማጥመቅ እንዳለባት የሚያዝ የመጽሐፍ ቅዱስ መርህ አለመኖሩን ያሳያል። ነገር ግን ግለሰቡ በኢየሱስ ካመነ በኋላ ኢየሱስን እንደ ደቀ መዝሙር ለመከተል መወሰኑን በይፋ መግለጹ ጠቃሚ ነው።

ለ. <u>ሁለተኛ፣</u> በሐዋርያት ሥራ 19:1-7 ጳውሎስ በመጥምቁ ዮሐንስ የተጠመቁትን ሰዎች እንደገና እንዳጠመቀ እንመለከታለን። እነዚህ አማኞች ዮሐንስ ባጠመቃቸው ጊዜ ስለ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ስለማያውቁ እውነተኛ ክርስቲያኖች አልነበሩም። ይህም አንድ ሰው በሕፃንነቱ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ፈቀቅ ባለች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተጠመቀ፣ ኢየሱስን ለመከተል በሚወስንበት ጊዜ፣ እንደገና መጠመቅ እንዳለበት የሚያመለክት ይመስላል።

ሐ. አዲስ ኪዳን ጥምቀት በቀዳሚነት አንድን ሰው የአንድ ቤተ እምነት አባል ለማድረግ የሚካሄድ ሥርዓት አድርጐ አይመለከተውም። ስለሆነም፣ በአንድ የወንጌል አማኞች ቤተ እምነት ውስጥ በኢየሱስ ላይ ያለውን እምነት ለመግለጽ የተጠመቀ ሰው ወደ ሌላ ቤተ እምነት በሚሄድበት ጊዜ እንደገና ማጥመቁ ተገቢ አይመስልም።

መ. በልጅነቱ የተጠመቀ ግለሰብ አዋቂዎችን የምታጠምቅ ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን በሚፈልግበት ጊዜ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸውን የጥምቀት ትርጉም እንዲያጠና ማበረታታቱ ተገቢ ይሆናል። መንፈስ ቅዱስ ግለሰቡ በኢየሱስ ማመኑን በጥምቀት እንዲገልጽ ከመራው ቤተ ክርስቲያን ውሳኔውን ልታከብርለት ይገባል። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ግለሰቡ እንደገና እንዲጠመቅ

ካልመራው በሌላ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት ለማግኘት ሲል እንደገና መጠመቅ የለበትም፡፡ ጥምቀት ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት የሚደረግ ሥርዓት አይደለምና፡፡

ሠ. በልጅነቱ ወይም ወንጌሉን ከመረዳቱ በፊት የተጠመቀ ሰው እንደገና ከተጠመቀ እንደገና የሚጠመቅበትን ምክንያት ለተመልካቾቹ በግልጽ ማብራራት አለበት፡፡ ይህም ሰዎች ጥምቀት ያድናል ብለው እንዳያስቡ ይረዳቸዋል፡፡ በተጨማሪም፣ እውነተኛ ክርስቲያን የሚጠመቀው በቤተ ክርስቲያናቸው የጥምቀት አስተሳሰብ ላይ ብቻ ተመሥርቶ አለመሆኑን ይገነዘባሉ፡፡

ረ. ክርስቲያናዊ ፍቅር ከጥምቀት ዝርዝር ጉዳዮች የበለጠ አስፈላጊ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ የጥምቀት አቋም ምንም ዓይነት ቢሆን፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለምእመናኗ የተለየ የጥምቀት አቋም ያላቸው ክርስቲያኖችም የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት እንደሆኑ መናገር ይኖርባታል፡፡ በክርስቶስ ወንድሞችና እኅቶች መሆናቸውን ተረድቶ የፍቅር አቀባበል ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

ሰይጣን ለብዙ ክፍለ ዘመናት የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለመከፋፈል በጥምቀት ጉዳይ ላይ የአስተሳሰብ ልዩነትን ሲፈጥር ቆይቷል፡፡ ማን ሊጠመቅ ይገባል? እንዴትስ ሊጠመቅ ይገባል? በሚሉት ክርክሮች ምክንያት የጥምቀት ትርጉም ብዙ ጊዜ ይዘነጋል፡፡ በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ብንለያይም ኢየሱስን ለማመንና ለመከተል የምናደርገው መሰጠት የበለጠ አንድነት እንዲያመጣልን እግዚአብሔር ይርዳን፡፡ ይሄም መሰጠት ጥምቀት ምን እንደሆነ በትክክል ከመረዳት ጋር ይሁንልን፡፡

# የውኃ
# ጥምቀት

